## ጋዜጣዊ መግለጫ

## አዋሽ ባንክ ለአንድ ወር የሚቆይ የዲጂታል ባንኪንግ ንቅናቄን አስጀመረ

አዋሽ ባንክ ከህዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ወር የሚቆይ ዋና መስሪያ ቤትን ጨምሮ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ "**ባንክዎን በእጅዎ**" በሚል መሪ ቃል የሚካሄድ የዲጅታል ባንኪንግ ንቅናቄን በይፋ አስጀምሯል።

የዲጂታል ባንኪንግ ንቅናቄዉ ሶስት ቁልፍ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን ታሳቢ ያደረገ ማለትም ፡-

1ኛ) አዋሽ ብር ፕሮ ሞባይል ባንኪንግ፣

2ኛ) አዋሽብር ፕሮ መርቻንት እና

3ኛ) የፖስ መርቻንት አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ እና ማነቃቃት ኢላማ ያደረገ መሆኑን የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ፀሃይ ሽፈራዉ ገልጸዋል።

አዋሽ ባንክ በኢትዮጵያ የባንክ ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመጠቀም ግንባር ቀደም ሆኖ ለመቀጠል ካለው ቁርጠኝነት አንፃር በሁሉም ቅርንጫፎች ላይ የዲጂታል አገልግሎትን እና አጠቃቀምን በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ በተለይም በአዋሽ ብር ፕሮ ሞባይል ባንኪንግ፣ በአዋሽ ብር ፕሮ መርቻንት፣ QR ኮድ እና በPOS ሶሎሽኖች ላይ በስፋትና በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ዋና ስራ አስፈጻሚዉ ተናግረዋል።

አዋሽ ብር ፕሮ ሞባይል ባንኪንግ አጠቃቀሙ ምቹና ቀላል ሆኖ የቀረበ ሲሆን፣ የአዋሽ ባንክ ተጠቃሚዎች አልግሎቱን በ7 የተለያዩ ቋንቋዎች ማለትም በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛ፣ በአፋርኛ፣ በአፍ ሱማሌ እና በ አፍ ሲዳሙ ቋንቋዎች መጠቀም እንዲችሉ ተደርጐ የተዘጋጀ ስለሆነ በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች አገልግሎት ይሠጣል ተብሏል። በተጨማሪም በተመሳሳይ መተግበሪያ የከወለድ ነፃ ባንኪንግ አገልግሎት ለኢኽላስ ተጠቃሚ ደንበኞቹ የቀረበ በመሆኑ መተግበሪያዉን ልዩ እንደሚያደርገዉም ገልጸዋል።

በዚህ የዲጂታል ባንኪንግ ንቅናቄ ባንኩ ለንቅናቄዉ ተዋናዮች አጓጊ የሆኑ የማበረታቻ ሽልማቶችን ያዘጋጀ ሲሆን

**1ኛ፣** ለአዋሽ ብር ፕሮ መርቻንቶች እና የፖስ መርቻንቶች በዲጂታል ባንኪንግ በንቅናቄዉ ወቅት እንደ አፈጻጸማቸው በየሳምንቱ 13 የሳምሰንግ እስማርት የሞባይል ቀፎዎች በአጠቃላይ 52 የሞባይል ቀፎዎች በስጦታ ይበረከታሉ።

**2ኛ፣** ለነጋዴዎች ገንዘብ ተቀባዮች ወይም ካሸሮች ደግሞ እንደየአፈጻጸማቸዉ እስከ ብር 15, 000.00 ሽልማት ሲያገኙ፤ደንበኞች አዲስ የአዋሽ ብር ፕሮ ሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚ ሲሆኑ እና ከዚህ በፊት አዋሽ ብር ፕሮ ሂሳብ ቁጥር ተከፍቶላቸው ለረጅም ጊዜ ሳይጠቀሙ ቆይተው በንቅናቄዉ ወቅት መጠቀም ለሚጀምሩ ደንበኞች ባንኩ የማበረታቻ የገንዘብ ስጦታ እንደሚያበረክት ተገልጿል።

ይህ የዲጅታል ባንኪንግ ንቅናቄ አዋሽ ባንክ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በማፋጠን፣ ለደንበኞች ወደር የለሽ ምቾት፣ ደህንነት እና ቅልጥፍና የተሞላበት አገልግሎት ለመስጠት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ንቅናቄዉ በመላ ኢትዮጵያ የላቀ የባንክ አጠቃቀም እንዲስፋፋ እንዲሁም በኢንዱስትሪዉ ለውጥ ለማምጣት የመዘጋጀቱ ማሳያ ነዉ በማለት ዋና ስራ አስፈጻሚዉ ንቅናቄዉን በይፋ አስጀመረዋል።

አዋሽ ባንክ

ህዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ


<u>ለበለጠ መረጃ</u>

ቺፍ - ዲጂታል ባንክንግ ኦፊሰር

ስልክ፡ +251-11-557-4566

ኢሚይል፡KefyalewS@awashbank.com